KANTAR

**Kantar South Africa**

**ግላዊነት እና የኩኪ መመሪያዎች ለዳሰሳ ጥናቶች** («መመሪያ»)
ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው፡- ማርች 2022

**መግቢያ**

የዳሰሳ ጥናቶች የሚደረጉት በKantar South Africa (Pty) Limited ነው

ደንበኞችን በመወከል የገበያ ጥናት የምናደርግ ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ ኃላፊነት የሚወስደው አካል ደንበኛው (በሌላ አጠራር ተቆጣጣሪ) ሆኖ እኛ እንደ አከናዋኝ (በሌላ አጠራር የውሂብ ከዋኝ) እንሰራለን።

ይህን የግላዊነት መመሪያ በጥንቃቄ እንዲያነቡት እንጠይቃለን።

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣ «የግል መረጃ» ሲባል በህይወት የሚኖርን ግለሰብ እና/ወይም ኩባንያ (አግባብነት ሲኖረው) የሚመለከት እና ይህንኑ ለመለየት የሚያገለግል መረጃ የሚል ትርጓሜ አለው

**ሕግን የተከተለ መሰብሰብ እና አጠቃቀም**

ይህ መመሪያ እርስዎ በመስመር ላይ፣ በአካል ፊት ለፊት በመገኘት፣ በፖስታ ወይም በስልክ አማካኝነት የዳሰሳ ጥናት ለእኛ ሲያደርጉ የሚሰጡን የግል መረጃ እንዴት እንደምንሰበስብ፣ እንዴት እንደምናስቀምጥና እንደምንጠቀም ማብራሪያ ይሰጣል።

የዳሰሳ ጥናቶችን በምናደርግበት ጊዜ፣ የእኛ ቃለ መጠይቅ አድራጊዎች/ግብዣዎች/መሰረተ ሥርዓቶች እና መጠይቆች እኛነታችንን በግልፅ የሚያሳውቁ እንዲሁም የምናነጋግርበትን ዓላማ(ዎች) እና ተፈጻሚነት በሚኖረው ጊዜ የግል መረጃ የምንሰበስብበትን ዓላማ የሚያብራሩ ናቸው። ማናቸውንም ጥያቄዎች አለመመለስ ወይም በዳሰሳ ጥናቱ ያለዎትን ተሳትፎ በማንኛውም ጊዜ ማቋረጥ ይችላሉ።

ስናነጋግርዎት፣ ብዙ ጊዜ በአካል፣ በስልክ፣ በኢሜይል ወይም በፖስታ፣ ከሚከተሉት ውስጥ ለአንዱ ዓላማ ይሆናል፡-

| **ሁኔታ** | **ዓላማ** | **የሚሰበሰበው/ የሚከወነው ውሂብ** | **ሕጋዊ መነሻ** |
|---|---|---|---|
| በዳሰሳ ጥናቶቻችን እንዲሳተፉ መጋበዝ | በእኛ የዳሰሳ ጥናቶች ለመሳተፍ ወካይ ናሙና ግለሰብ የመሆን ዕድል ለመስጠት | የተደወለበት ስልክ ቁጥር (በዘፈቀደ የሚደወል)፣ ፖስታ አድራሻ፣ ኢሜይል አድራሻ። | ምክንያታዊ የሆነ ፍላጎት ወይም ፈቃደኝነት<br>(ተፈፃሚ የሚሆን ከሆነ)<br><br>ወካይ ናሙና ግለሰቦች በዳሰሳ ጥናቶቻችን እንዲሳተፉ ለመጋበዝ እንድናነጋግር የሚያስችለን በቂ ምክንያታዊ ፍላጎት አለን።<br><br>Kantar ወይም ደንበኛው ለእርስዎ በዳሰሳ ጥናት እንዲሳተፉ ግብዣ ለማቅረብ እንድናነጋግርዎት ፈቃድዎ አለው። |
| የዳሰሳ ጥናቶች | የተወሰኑ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በሚመለከት ዕይታዎችዎን ለመረዳት ወይም በተለያዩ ሁኔታዎች የእርስዎን ባህሪ ለመረዳት።<br>በቅርቡ ባካሄድነው የዳሰሳ ጥናት ላይ የሰጧቸውን ምላሾች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ።<br>ተሳትፎን ለማስተዳደር፣ ለምሳሌ የሽልማት ዕጣዎችን፣ ማካካሻዎችን እና ቅድመ-ክንውኖችን ወዘተ።<br>ተሳታፊዎችን በድጋሚ ለማነጋገር፣ ለምሳሌ ቀጣይነት | ልዩ መለያዎች፣ የመገኛ ዝርዝሮች፣ ኢሜይል አድራሻ፣ ድምፅ፣ ምስል፣ አስተያየት | የግል መረጃዎን ለመጠቀም የእርስዎን ፈቃድ በጠየቅንበት የዳሰሳ ጥናት በፈቃደኝነት መሳተፍ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ላላቸው ወይም ክትትል ለሚፈልጉ የዳሰሳ ጥናቶች። | | |
| ማጭበርበርን መከላከል | የንግድ ፍላጎቶቻችንን ከማጭበርበር ባህሪ መከላከል | አይፒ አድራሻ፣ የአሳሽ መስፈርቶች፣ የመሣሪያ መስፈርቶች፣ የፖስታ አድራሻዎች፣ ኢሜይል አድራሻዎች | አግባብነት ያላቸው ፍላጎቶች – ንግዳችንን ከማጭበርበር ወይም ከሌሎች የሚከለከሉ ባህሪያት ለመከላከል አግባብ የሆነ ፍላጎት አለን። |
| የዳሰሳ ጥናቶች ተሳትፎ ልዩ መሆን | በአንድ ግለሰብ ብዙ የዳሰሳ ጥናቶች እንዳይገቡ መከላከል | አይፒ አድራሻ፣ የአሳሽ መስፈርቶች፣ የመሣሪያ መስፈርቶች | አግባብነት ያላቸው ፍላጎቶች – በአንድ ግለሰብ ብዙ ግብዓቶች እንዳይኖሩ ለመከላከል አግባብ የሆነ ፍላጎት አለን። |
| የውሂብ ማዛመድ እና ማበልፀግ | የእርስዎን የግል መረጃ ከሌሎች የውሂብ ምንጮች እና በውሂብ ማስተዳደር ልዩ ሙያ ካላቸው ሦተኛ ወገኖች ጋር በማዛመድ እርስዎን የሚመለከተውን በፋይል የምንይዘውን ውሂብ እናበለጽጋለን። | ልዩ መለያ፣ የመገኛ ዝርዝሮች፣ ኢሜይል አድራሻ፣ ማህበራዊ መግቢያ፣ ኩኪ፣ የሞባይል መሣሪያ መታወቂያ | የግል መረጃዎን ለመጠቀም የእርስዎን ፈቃድ በጠየቅንበት የዳሰሳ ጥናት በፈቃደኝነት መሳተፍ። |
| የስልክ የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን ማስተዳደር | አንድ ግለሰብ በድጋሚ በስልክ እንዳይደወልላቸው ጥያቄ ካቀረቡ፣ ይህን ለማድረግ ዝርዝራቸውን እንይዛለን። | ስም እና ስልክ ቁጥር | አግባብነት ያላቸው ፍላጎቶች – የግለሰብን ጥያቄ ለማሟላት መረጃውን ለመያዝ የሚያስችለን አግባብነት ያለው ፍላጎት አለን። |

ራሳችንን ወይም የምንሰራውን ሥራ በውሸት ቀይረን የምንቀርብበት ሁኔታ ፈፅሞ የለም። ከእኛ እንደሆነ የሚያስመስል እርስዎን የሚመለከት ኢሜይል ከደረሰዎት፣ እባክዎ ከታች እንዴት እኛን ማነጋገር እንደሚቻል በተመለከተው መንገድ ያነጋግሩን።

በስልክ፣ በፖስታ፣ በአካል ወይም በመስመር ላይ በሚከተሉት መንገዶች የዳሰሳ ጥናት በማድረግ እንዲሳተፉ አነጋግረንዎታል

- ✦ በዘፈቀደ የቤትዎን በር በማንኳኳት
- ✦ የዘፈቀደ ቁጥር መደወያዎች (RDD) በመጠቀም በዘፈቀደ ወደ ቁጥርዎ በመደወል
- ✦ ከአሁን ቀደም ከተመዘገቡበት፣ ምርቶቹን ወይም አገልግሎቶቹን ከተረከቡት ወይም በአጠቃላይ መስተጋብር ከነበረዎት እና አሁን የዳሰሳ ጥናት ከምናደርግለት የእኛ ደንበኛ የእርስዎን የመገኛ ዝርዝሮች በማግኘት
- ✦ ናሙና ከናሙና አቅራቢ በመግዛት
- ✦ የእርስዎን መረጃ በይፋ ከሚገኙ ምንጮች በማግኘት
- ✦ የመገኛ መረጃዎን ከእርስዎ ጋር ግንኙነት ከነበረው ቀጣሪ በማግኘት
- ✦ ወይም በተጨማሪ የዳሰሳ ጥናቶች ለመሳተፍ በድጋሚ እንድናነጋግርዎት ቀደም ሲል ተስማምተዋል

**ሦስተኛ ወገኖች እና በድንበሮች መካከል የውሂብ ማስተላለፍ፡-**

ከላይ ለተገለጸው ዓላማ የግል መረጃ እንሰበስባለን፣ ነገር ግን የግል መረጃዎን ለሦስተኛ ወገኖች አናጋራም ወይም አንሸጥም፣ በሕግ ካልተጠየቀ ወይም በሌላ መልኩ ካልተስማሙ በስተቀር።

የእርስዎ የግል መረጃ በKantar ቡድን ውስጥ በሚገኙ እህት ኩባንያዎች፣ ወይም በ3ኛ ወገን አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ከዳሰሳ ጥናቱ ጋር ለተያያዙ እንደ የውሂብ ክንውን፣ የሽልማት ዕጣን ማሟላት ወይም ሌሎች ማካካሻዎችን የመሳሰሉ ዓላማዎች በእርስዎ የመኖሪያ አገር ውስጥ ወይም ውጭ ሊሰበሰብ፣ ሊከማች፣ ሊተላለፍ ወይም ሊከወን ይችላል። ሁሉም ወገኖች ማናቸውንም የሚሰበስቡትን ወይም ለእኛ የሚያጋሩትን መረጃ ወይም እኛ የምንሰበስበውን እና ለእነርሱ የምናጋራውን መረጃ በሚስጥር

እንዲይዙ እና በእኛ ልክ የሚገኙ የደህንነት መስፈርቶችንና ተግባሮችን ተከትለው እንዲጠብቁ የውል ስምምነት አለባቸው። የግል መረጃዎ ከሚኖሩበት አገር ውጭ ወደሆነ ግዛት (አግባብ ሲሆን) ከተላለፈ፣ ከተከማቸ ወይም ክንውን ውስጥ ከገባ እና ያ ግዛት በቂ የግል መረጃ ጥበቃ ደረጃ እንደማያቀርብ ከታወቀ፣ በቂ የሆነ የሕግ መስፈርት እናስቀምጣለን። ለምሳሌ፣ መደበኛ የፀደቁ የውል አንቀፆች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናት፣ አስገዳጅ የኮርፖሬት ህጎችን ወይም ሌሎች በቡድን መካከል ያሉ ሂደቶችን ተፈጻሚ አድርገው ከሚሰሩ አካላት ጋር በመስራት፣ የግል መረጃን ለማስተላለፍ የእርስዎን ፈቃድ ማግኘት፣ ማስተላለፉ በመካከላችን ያለውን ውል ለመፈጸም አስፈላጊ ሲሆን ወይም ውሉ እርስዎን በመወከል የተገባ ሲሆን፣ ወይም ማስተላለፉ የህግ ጥያቄዎችን ለመመስረት፣ ለመፈጸም ወይም ለመከላከል አስፈላጊ ሲሆን።

**ሚስጥራዊነት፣ ደህንነት እና የኢንዱስትሪ መስፈርቶች፦**

የእርስዎን የግል መረጃ ለመጠበቅ እና የግል መረጃዎ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንደሚከወን የሚያስፈልጉ ምክንያታዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ አግባብነት ያላቸው የቴክኖሎጂ እና የመዋቀር እርምጃዎች አሉን። የሚያቀርቡት መረጃ በሙሉ ደህንነታቸው በተጠበቁ አገልጋዮች እና አካባቢ ይቀመጣል። አጋጣሚ ሆኖ፣ ማንኛውም የውሂብ ማስተላለፍ 100% ደህንነቱ የተጠበቀ እንደሚሆን ዋስትና የለም። በመሆኑም፣ እኛ የግል መረጃዎን ለመጠበቅ ጥረት ስናደርግ፣ ወደ እኛ የሚያስተላልፉት ወይም ከመስመር ላይ ምርቶቻችን እና አገልግሎቶቻችን የሚተላለፍ መረጃን ደህንነት በሚመለከት ማረጋገጫ ወይም ዋስትና አንሰጥም፣ እናም ይህን የሚያደርጉት በራስዎ ኃላፊነት ነው። የእርስዎን መረጃ ማስተላለፍ ከተረከብን በኋላ፣ ስርዓቶቻችን ደህንነታቸው የተጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ ምክንያታዊ የሆኑ እርምጃዎችን እንወስዳለን።

ሁሉም የእኛ የሦስተኛ ወገን ተዋዋይዎች፣ የጣቢያ ላይ አገልግሎት አቅራቢዎች እና ሰራተኞች ምስጢር መጠበቅን፣ ደህንነትን እና ግላዊነትን በሚመለከት መመሪያዎቻችንን እና የአሰራር ሂደቶቻችንን እንዲከተሉ የውል ግዴታ አለባቸው።

የሚከተሉትን የኢንዱስትሪ መስፈርቶች እንከተላለን፦

- GDPR፣ የዩናይትድ ኪንግደም የውሂብ ጥበቃ ድንጋጌ 2018፣ የአውሮፓ ህብረት GDPR፣ የ2013ቱ የግል መረጃ ጥበቃ ድንጋጌ 4፣ ማናቸውም አግባብነት ያላቸው የአካባቢ የውሂብ ጥበቃ ህጎች እና ማናቸውም ከጊዜ ወደጊዜ ሊሻሻሉ የሚችሉ ተዛማጅ ድንጋጌዎች
- MRS እና ESOMAR የሙያ ስነ ምግባርን እንከተላለን

በአንድ የዳሰሳ ጥናት ላይ የእርስዎን የዳሰሳ ጥናት ምላሾች ከሌሎች ተሳታፊዎች ምላሾች ጋር እናዋህደውና ያንን የተዋሃደ ምላሽ ጥናቱን ለሚያስደርገው አካል ሪፖርት እናደርጋለን፣ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑት ካልተከሰቱ በስተቀር።

የግል መረጃዎን ወይም የዳሰሳ ጥናት ምላሾችዎን ለሦስተኛ ወገኖች የምናስተላልፍባቸው ብቸኛ ልዩ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው

- የእርስዎን ማንነት የሚያሳይ መረጃ እና/ወይም የግል ምላሾችን ለተጠቀሰ ዓላማ ለሦስተኛ ወገን ለማጋራት ከጠየቁ ወይም ከተስማሙ።
- ይፋ የተደረገላቸውን መረጃ በሚስጥር እንዲይዙ እና መረጃዎን ለምርምር ወይም ለስታቲስቲክሳዊ ዓላማዎች ብቻ እንዲጠቀሙ የውል ግዴታ ላለባቸው ሦስተኛ ወገን አከናዋኞች ምላሾችዎን ስናጋራ

**የኩኪዎች ይፋ መሆን (ለመስመር ላይ የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች ብቻ)፦**

ኩኪዎች የተጠቃሚ መለያ ቁጥር በመስጠት የእርስዎን የመስመር ላይ አሰሳ የሚመለከት የተወሰነ መረጃን በድር ጣቢያ አማካኝነት በኮምፒዩተርዎ ወይም በመሣሪያዎ ላይ የሚያስቀምጡ አነስተኛ የፅሁፍ ፋይሎች ናቸው። ተጠቃሚዎች ድር ጣቢያዎችን በውጤታማነት እንዲያስሱ እና የተወሰኑ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ለማገዝ በድር አልሚዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ። ድር ጣቢያዎች

KANTAR

የተወሰኑ መረጃዎችን ለአሳሽ ይልካሉ፣ እነዚህም የፅሁፍ ፋይል ይፈጥራሉ። ተጠቃሚው ወደዚያ ድር ጣቢያ ሲመለስ፣ አሳሹ ይህን ፋይል በማውጣት ወደ የድር ጣቢያ አገልጋዩ ይልካል።

በመደበኛ የመስመር ላይ የውስጥ ዳሰሳ ጥናቶች ላይ ኩኪዎችን አንጠቀምም። ኩኪዎች በአጋር መሰረተ ስርዕት የሚያስፈልጉ ሲሆኑ፣ በመሰረተ ስርዓቱ የግላዊነት ማሳወቂያ/መመሪያ አማካኝነት ይህን እንዲያውቁ ይደረጋል።

የባህሪ ክትትል የዳሰሳ ጥናቶችን ለማድረግ፣ የግድ ያልሆኑ ኩኪዎችን / የሶፍትዌር መተግበሪያዎችን እንጠቀማለን፣ ነገር ግን ይህን የምናደርገው ለእንደዚህ ዓይነት ኩኪዎች / መተግበሪያዎች <u>በግልፅ ከተስማሙ</u> ብቻ ነው።

ይህ ለአብዛኞቹ የመስመር ላይ የዳሰሳ ጥናቶች የሚሰራ በመሆኑ፣ የተወሰኑ መረጃዎችን በራስሰር በመሰብሰብ በዳሰሳ ጥናቱ ውሂብ ፋይሎች ውስጥ እናስቀምጣለን። ይህ መረጃ እንደ ኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ (አይፒ አድራሻ)፣ የአሳሽ ዓይነት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢ (አይኤስፒ)፤ የጠቋሚ/መውጫ ገፆች፣ ስርዓተ ክወና እና ቀን/ሰዓት የመሳሰሉትን ነገሮች ያካትታል።

ይህን በራስሰር የተሰበሰበ መረጃ እንደ የአሳሽ አጠቃቀም የመሳሰሉ አዝማሚያዎችን ለመተንተን እና ጣቢያውን ለማስተዳደር፣ ለምሳሌ የአሳሽዎን ዓይነት መነሻ በማድረግ የዳሰሳ ጥናቱን የተሳለጠ ለማድረግ እንጠቀምበታለን። በተጨማሪም የአይፒ አድራሻዎን ከዚህ የአይፒ አድራሻ ብዙ ተሳታፊዎች በዳሰሳ ጥናቱ የተሳተፉ ስለመሆኑ ለመፈተሽ ልንጠቀምበት እንችላለን።

**ትክለኛነት፡-**

የግል መረጃዎን በቅርብ የሰጡንን መረጃ መነሻ በማድረግ ትክክለኛ፣ የተሟላ፣ ወቅታዊ እና አስፈላጊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ ሁሉንም ምክንያታዊ እርምጃዎች እንወስዳለን። የግል መረጃዎን ለማዘመን ከፈለጉ፣ እባክዎ ከታች የቀረቡ ዝርዝሮችን በመጠቀም ያነጋግሩን።

የግል መረጃዎ ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ወቅታዊ ሆኖ እንዲቀጥል ጥያቄዎቻችንን በታማኝነት በመመለስ በእርስዎ እገዛ ላይ እንመሰረታለን፣ እንዲሁም በግል መረጃዎ ላይ የሚኖሩ ለውጦችን የሚመለከተው አካል (እኛ ወይም - ብዙ ጊዜ - ደንበኞችን) እንዳወቀ ማረጋገጥ የእርስዎ ኃላፊነት ነው።

**የልጆችን ውሂብ መሰብሰብ፡-**

ከ18 ዓመት በታች ያሉ ልጆች ስምምነት ሳይኖር በዳሰሳ ጥናት እንዲሳተፉ እያወቅን ግብዣ አናቀርብላቸውም። ከ18 ዓመታት በታች ያሉ ልጆችን በቀጥታ ማሳተፍ በሆነ ፕሮጀቶች ውስጥ ማሳተፍ ቢያስፈልግ እና ተገቢ ቢሆን፣ ኃላፊነት ያለበት ጎልማሳ ሰው ፈቃድ የሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ እርምጃዎችን እንወስዳለን። የልጆችን የግል መረጃ አንሸጥም።

**ልዩ የመረጃ አሰባሰብ፡-**

በዳሰሳ ጥናታችን «ልዩ ምድቦች» በሚል የሚከፈሉ የግል መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥያቄ ልናቀርብ እንችላለን። እነዚህም የዘር ወይም የጎሳ ማንነት፣ የፖለቲካ አተያይ፣ ኃይማኖት ወይም ፍልስፍናዊ እምነት ወይም የንግድ ማህበር አባልነት፣ የጀነቲክ ውሂብ፣ አንድን የተፈጥሮ ሰው ልዩ ማንነት ለማወቅ የሚያስችል ስነ-ህይወታዊ ውሂብ፣ የጤና ሁኔታን የሚመለከት ውሂብ ወይም የተፈጥሮ ሰውን ፆታዊ ህይወት ወይም ፆታዊ ዝንባሌ የሚመለከት ውሂብ የመሳሰሉትን ያካትታሉ። ይህን ውሂብ እንደተገለፀው እንድንጠቀምበት ለእኛ መስጠት ሁልጊዜም የእርስዎ ምርጫ ይሆናል።

**የግለሰቦች መብቶች፡-**

እርስዎን በሚመለከት ለምንይዘው ውሂብ መዳረሻ ለመጠየቅ፣ ከታች «እኛን እንዴት ማግኘት ይቻላል» በሚለው ስር ለቀረበው ኢሜይል ወይም የፖስታ አድራሻ ጥያቄዎን በፅሁፍ ማስገባት ያስፈልግዎታል። ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ ጥያቄውን እያቀረቡለት ያለውን የKantar ምድብ (እና ለምሳሌ የፓናሊስት መታወቂያ ወይም ሌላ መለያ) ማመልከት ያስፈልግዎታል።

በእኛ መዝገብ ውስጥ የሌለን የኢሜይል አድራሻ ወይም ሌላ የመገኛ ዝርዝር በመጠቀም መልዕክት ከላኩልን፣ በተጨማሪነት በመንግስት የተሰጠ የሚሰራ ይፋዊ መለያ (ለምሳሌ የመንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት) ቅጂ እንዲያቀርቡልን እንጠይቃለን።

የግል መረጃዎን በሚመለከት የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፦

- ሀሳብዎን የመቀየር እና ስምምነትዎን ማንሳት መብት
- የግል መረጃዎን የማግኘት መብት
- የግል መረጃዎን የማስተካከል መብት
- የግል መረጃዎን ከእኛ ስርዓቶች ላይ የማጥፋት መብት፣ መረጃዎን በሂደት ውስጥ እንድናስቀጥል አግባብነት ያለው ፍላጎት ያለን ካልሆነ በስተቀር
- የግል መረጃዎን ወደ ውጭ የማስተላለፍ (ወደ ውጭ የማስተላለፍ መብት)
- የግል መረጃዎን ክንውን የመገደብ መብት
- የግል መረጃዎን ክንውን የመቃወም መብት
- አግባብነት ባላቸው የውሂብ ጥበቃ ህጎችን መነሻ በማድረግ ያሉዎትን ማናቸውንም መብቶች በመጠቀምዎ ምክንያት መድሎ ያለማጋጠም መብት

አስፈላጊ ከሆነ፣ እንደ አቅራቢዎቻችን ወይም አገልግሎት ሰጪዎቻችን የመሳሰሉ፣ የእርስዎን የግል መረጃ ያስተላለፍንላቸው አካላትን በጥያቄዎ መሰረት ለውጦች ስናደርግ ልናሳውቃቸው እንችላለን። ከእነዚህ የሦስተኛ አካላት ጋር መረጃ ስንለዋወጥ፣ የእርስዎን ጥያቄ ለመመለስ በእነዚህ ሦስተኛ አካላት ለሚወሰዱ ማናቸውም እርምጃዎች እኛ ኃላፊነት የለብንም። በእነዚህ ሦስተኛ ወገን የተያዘ የግል መረጃዎችን መድረስ እንዲሁም ትክክል በማይሆን ጊዜ ማስተካከል፣ መቀየር ወይም መሰረዝ ይችላሉ።

**ውሂብ ማስቀመጥ እና መያዝ፦**

የግል መረጃ የሚያዘው የታሰበውን እና በህግ የሚፈቀደውን አጠቃቀም ተፈጻሚ ለማድረግ እስከሚያስፈልግበት ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ በዚህ ሁኔታ፣ በህግ የሚያስገድድ ሁኔታ ከሌለ በስተቅር፣ ውሂብ ከ12 ወራት ለረዘመ ጊዜ አንይዝም። የማያስፈልግ የግል መረጃ ሚስጥራዊነትን በማያጋልጥ መልኩ ይወገዳል።

በኩባንያ የንግድ ቀጣይነት ዕቅድ መሰረት እና በ ISO 27001፣ ISO 9001፣ ISO 20252 ማረጋገጫዎች በሚጠየቀው መሰረት፣ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ደግሞ በህግ፣ የኤሌክትሮኒክ ስርዓቶቻችን መጠባበቂያ እየተወሰደባቸው ውሂባቸው ይቀመጣል። እነዚህ መጠባበቂያዎች ጥብቅ ቁጥጥር በሚደረግበት አካባቢ ለተወሰነ የጊዜ ገደብ ይያዛሉ። የጊዜ ገደባቸው ካለፈ በኋላ፣ ውሂቡ ይሰረዛል፣ እንዲሁም ውሂቡ ሙሉ በሙሉ መጥፋቱን ለማረጋገጥ አካላዊ ማስቀመጫው ይወድማል።

**ጉልህ ለውጦች ሲደረጉ ማሳወቅ፦**

የግላዊነት መመሪያችን ላይ መደበኛ ክለሳ እናደርጋለን እንዲሁም ከጊዜ ወደጊዜ ማሻሻያዎችን ልናደርግ እንችላለን። ሁልጊዜም ቢሆን በጣም የቅርብ ጊዜውን መመሪያ በዚህ ገፅ ላይ እናስቀምጣለን። መመሪያው ለመጨረሻ ግዜ ሲሻሻል መዝግበን እንይዛለን።

የተፈጠረበት ቀን፦ 13/06/2011
ለመጨረሻ ጊዜ የተከለሰው፦ 28/09/2021

KANTAR

**ራስሰር ውሳኔ መስጠት / መለየት፦**

በአንዳንድ ሁኔታዎች እርስዎን በሚመለከት ራስሰር የሆነ ውሳኔ ወይም መለየት ልናከናውን እንችላለን። ነገር ግን፣ አብዛኛውን ጊዜ እርስዎን የሚመለከቱ ጉልህ የህግ ውሳኔዎች የሚያስከትሉ አይደሉም። እርስዎን በሚመለከት በራስሰር የተወሰዱ ህጋዊ ፋይዳ ያላቸው ውሳኔዎችን ይግባኝ የማለት መብት አለዎት። ይህን በሚመለከት ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ ያነጋግሩን።

**እንዴት ሊያነጋግሩን ይችላሉ፦**

የግል መረጃዎን ስለምንከውንበት ሂደት ደስተኛ ካልሆኑ፣ ያንን የምናስተካክልበት ዕድል እንድናገኝ እንፈልጋለን። በ PrivacyRSA@Kantar.com ሊያነጋግሩን ይችላሉ። በተጨማሪም፣ የእኛ የውሂብ ጥበቃ ባለሙያ የሆኑትን Ravinder Roopra፣ በDataProtection@Kantar.com ማነጋገር ይችላሉ። የእኛ የውሂብ ጥበቃ ባለሙያ የውሂብ ጥበቃ ህጎችን እና የግላዊነት መመሪያዎቻችንን እያከበርን መሆኑን የሚከታተሉ ሲሆን፣ ክትትል ለሚያደርጉ ባለስልጣናት የግል መረጃን በማከናወን ሂደት ላይ ቀዳሚ ተጠሪ ሰው ናቸው።

**ቅሬታዎች እና ለተወሰኑ አገራት ልዩ የሆኑ ይፋ ማውጣቶች፦**

የግል መረጃዎን ስለምንከውንበት ሂደት ደስተኛ ካልሆኑ፣ ያንን የምናስተካክልበት ዕድል እንድናገኝ እንፈልጋለን። እባክዎ info@kantar.com ላይ ያነጋግሩን እና የሆነ ሰው ያነጋግርዎታል። ነገር ግን፣ እንደ የመረጃ ተቆጣጣሪ ለመሳሰሉት እና ዝርዝራቸው https://www.justice.gov.za/inforeg/contact.html ላይ ለሚገኙ ባለስልጣናት ቅሬታ የማቅረብ መብት የለዎትም

የKantar ቡድን ኩባንያ ነን። የተመዘገበ ስማችን እና ስማችን Kantar South Africa (Pty) Limited, 4 Roggebaai Place, Foreshore, Cape Town 8001